# “ድርሳነ–ወሐቢያን” በወፍ በረር ዕይታ

(ማጠቃለያ)

አብዱልአዚዝ ከድር 8/14/12

ባለፉት አራት ተከታታይ ፅሑፎቼ አብዛኛውን የድርሳኑን ክፍል በወፍ በረር ዕይታ በመቃኘት፤ የሰነዱን ባዶነት ለውድ አንባቢዎቼ በማሻማ ሁኔታ ለማሳየት ሞክሬያለሁ። በዚህም አንባቢያን በወሐቢያው አቀንቃኝ የተሰናዳው ጥራዝ ምንም ዓይነት ተጨባጭ ዕውነት የሌለው፣ በ‘እንዲህ ሊሆን ይችላል’ መላ-ምታዊ ቃላት የታጀለና በዋነኛነት በሃይማኖታዊ ጉዳይ ላይ ሳይሆን፣ መንግስታዊ ተግባራትን በማጣጣል ላይ ያነጣጠረ መሆኑን ግንዛቤ እንደያዛችሁ አልጠራጠርም። በዛሬው ፅሑፌ ደግሞ የሰነዱን ቀሪ ክፍል እንዲህ እንመለከተዋለን።

ድርሳኑ በቀሪዎቹ ገፆቹ ላይም ተመሳሳይ የቃላት ድረታን ከመጠቀም አልቦዘነም፡፡ …‘እገሌና እገሌ የሚባሉ አገራት ሐይማኖታዊ ቁርኝት አላቸው፡፡ ይህ ደግሞ በእስልምና ላይ የተመዘዘ ዶሴ ነው’ የሚሉ ግለሰባዊ ጥንቆላ መሳይ ተአማኒነት የጎደላቸው ንግርቶችን ከኢንተርኔት በመገልበጥና እንደምንም ጉዳዩን አጣሞ ከሀገራችን ጋር ለማያያዝ ይጥራል፡፡ ይህን መሰልን የማደናገር ስልት የሚጠቀመው ሰነዱ፤ የተለያዩ ሐገራትን የኋላ ታሪክ ከመጠን በላይ ለጥጦ በመተንተን ‘ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ እንዲህ ለማድረግ አስባለች’ በሚል የ‘ይሆናል’ አስተሳሰብ ህዝበ-ሙስሊሙን በቅጥፈት ለማታለል የተሰናዳ መሆኑን የጠቃቀሳቸውን ‘አርቲ ቡርቲ’ ወሬዎችን በማየት መረዳት እንችላለን።

በአቶ አብደላህ አደም የተዘጋጀው ሐይማኖታዊ የፖለቲካ ንግድ ድርሳን ማስረጃው ምን እንደሆነ ባይታወቅም፤ “መጪዋ ኢትዮጵያ የሙስሊሞች የጭቃ ውስጥ እሾህ እንድትሆን ይፈለጋል፣ ነባሩ እስልምና መብቱን የማይጠይቅ ነው፣ የሙስሊሞች እምነት እንደኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ‘የኢትዮጵያ ብቻ’እንዲሆን ይፈለጋል፣ ተማሪዎችና የመንግስት ሰራተኞች ትምህርትንና ስራን ያስተጓጉላል በሚል በሮመዳን ወቅት እንዳይፆሙ ሊደረጉ ይችላሉ።…” የሚሉ እጅግ አሳፋሪና በምናብ የተቀነባበሩ ቅጥፈቶችን ከትቦ እናገኛለን። ግና ‘ይህ እሳቤ እውነት እኛ በምንገኝባት ኢትዩጵያ ውስጥ አለን?’ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይመስለኛል።

እስቲ ይህን ጥያቄ ይዘን ወደ ገሃዱ ዓለም ዕውነታ እንመለስ። እንደሚታወቀው የየትኛውም ሀገር መንግስት የሚመራው ሀገር ለዜጎቹ መጪው ጊዜ ብሩህ እንዲሆን የመሻቱ ጉዳይ አጠያያቂ አይደለም። ሆኖም ይህን ዕውን ለማድረግ ሀገሪቱ ለዚህኛው ሃይማኖት ተከታይ የተመቸች፣ ለዚያኛው ደግሞ የምትጎረብጥ እንድትሆን በማሰብ መፈፀም አይቻልም። ምክንያቱም ሀገሪቱ በልማት በልፅጋ መጪውን ለዜጎች ብሩህ ማድረግ የሚቻለው አጠቃላይ ህዝቡን ከዳር እስከ ዳር በማነቃነቅ በየደረጃው በልማቱ ላይ ተሳታፊ እንዲሆን እንጂ፤ የወሐቢያው ድርሳን ለማደናገር እንደሚሞክረው የዕድገት ሃይል የሆነውን ህዝብ በሃይማኖት በመነጣጠል አይደለም።

ለነገሩ የኢትዩጵያ መንግስትም ይሁን ገዥው ፓርቲ ከአመጣጣቸው ጀምሮ ህዝብን እንደ ህዝብ በማክበር ተግባራቸውን በህዝቡ ጉያ ውስጥ ሆነው ሲከውኑ የመጡ ናቸው። የቀደምት ድላቸውም ሆነ በአሁኑ ወቅት እየተመዘገበ ላለው ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት ወሳኙ ሃይል ህዝብ መሆኑን ስለሚገነዘቡ ማናቸውንም ፍፃሜዎቻቸውን ከሃይማኖት አኳያ ሊለኩት አይችሉም፤አድርገውትም አያውቁም።

ለዚህም ነው ገዢው ፓርቲ በዲሞክራሲያዊ ፓርቲ በሚወዳደርበት ወቅት “መጪው ጊዜ ከእኔ ጋር ብሩህ ነው የሚለው”፡፡ ግና የዋሕብያው ቡድን “የአብዬን ወደ እምዬ” እንዲሉ የራሱን ፍላጎት በግድ

በመንግስት ላይ ሊያላክክ በመፈለጉ “ጅብ የማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ” የሚባለውን ይትባህል የሚያስታውሰን ከመሆን የዘለለ አይሆንም፡፡

ኸረ ለመሆኑ በሀገር ውስጥ ያሉትን ሐይማኖቶች በማጥላላት ብሎም የገዛ እምነትን ‘ነባሩ እስልምና ለዘብተኛና መብቱን የማይጠይቅ ነው’ እያለ ለመከፋፈል የሞከረው መንግስት ነው ወይስ የወሐቢያ አቀንቃኞች?፣ መጪው ጊዜ ለሌሎች የሀገራችን እምነት ተከታይ ዜጎች ጨለማ እንዲሆን የራሱን አመለካከት በሃይል ለመጫን የሚቋምጠው ከቶ ማን ይሆን?–አዎ! እንደ እውነቱ ከሆነ ዜጎች የያዙትን ዕምነት እየከፋፈለ የሚያጥላላው እንዲሁም መጪው ጊዜ ለሌሎች እምነት ተከታዩች አስቸጋሪ እንዲሆን ሁከትን በስልትነት ተከትሎ የሚንቀሳቀሰው አቶ አብደላህ የሚገኙበት የፅንፈኞች ስብስብ ነው።

እናም መጪው ጊዜ ለነውጠኞቹ ወሐቢያውያን ካልሆነ በሰተቀር ለሰላም ወዳጹ ህዝበ-ሙስሊም ብሩህ ነው። ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ውስጥ እየጎለበተ የመጣው ምህዳር ከሰላም ውጪ የነውጥ ቋያን አንግበው ለሚንቀሳቀሱ እፍኝ ሃይሎች የሚመች ባለመሆኑ ነው። ስለሆነም የወሐቢያ ደቀ-መዝሙሮች የራሳቸውን እኩይ ሴራ በህዝበ-ሙስሊሙ ስም በማስታከክ ሀገራችን ለሙስሊሙ “የጭቃ ውስጥ እሾህ ትሆናለች” የሚል ጩኸታቸው ለራስ ከወረደ ሞሾ ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ለምን ቢባል፤ የነገዋ ኢትዩጵያ የጭቃ ውስጥ እሾህ ልትሆን የምትችለው ለሁከትና ብጥብጥ ናፋቂዎች ብቻ ስለሆነ ነው።

በአዲሲቷ አትዩጵያ ውስጥ ማንኛውም ዜጋ ሰብዓዊም ይሁን ዴሞክራሲያዊ መብቱ ተከብሮለታል። መብቶቹን የመጠየቅና የማስከበር ህገ-መንግስታዊ ዋስትናም አለው። ይህን የመብት ማስከበር ተግባሩንም ላለፉት ሃ አንድ ዓመታት ሲያጣጥመው መጥቶ ዛሬ ላይ ደርሷል።ይሁንና “ድርሳነ-ወሐቢያ” ራሱ ነባሩ እስልምና ያለውን እምነት “መብቱን የማይጠይቅ ነው” በሚል የከፋፍለህ አጥላላ ስሌት ሊኮንነው ይፈልጋል። በመሰረቱ እኔም ሆንኩ ሌሎቸ የእምነቱ ተከታዩች በግልፅ እንደምናውቀው፤ሃይማኖታዊ መብቶቻችንን በአግባቡ ስንጠይቅ መጥተናል። በዚህም ከሌሎች ስርዓቶች ታይቶ በማይታወቅ መልኩ የጠየቅነው ጥያቄ ምላሽ ተነፍጎት አያውቅም።

ለአብነት ያህል ባለፉት ሁለት አስርታት ውስጥ የመስጂድ መስሪያ ቦታዎችን ጠይቀን ሙሉ በሙሉ ምላሽ አግኝተናል። ታዲያ እነዚህ መስጂዶች የተገነቡት ማን ጠይቆ ነው?–የወሐቢያ የነውጥ አቀንቃኞች ናቸው ወይስ ጨለምተኛው ፀሐፊ?–እርግጥም መብቱን ጠይቆ አጥጋቢ ምላሽ የተሰጠው ኢትዩጵያ ውስጥ ያለው የሙስሊሙ እምነት እንጂ፤ሃይማኖቱን ለባዐዳን መጤዎች በመሸጥ ለገንዘብ ያጎበደደው አክራሪ ቡድኑ አይደለም። እናም የ“ድርሳነ-ወሐቢያ” ረብ የለሽ ሰበካ በየትኛውም መስፈርት ሚዛን የሚደፋ አይደለም።

በድርሳኑ ከታቢ የቀረበው ሌላኛው ልቦለዳዊ ድርሰት “የሙስሊሞች እምነት እንደ ኢትዩጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ‘የኢትዩጵያ ብቻ’እንዲሆን ይፈለጋል” የሚል ነው። እርግጥ የወሐቢያው ጋሻ ጃግሬ ይህን አስቂኝ ተረት ከየት እንዳመጡት የሚያውቀት እርሳቸውና ሸይጣን ብቻ ቢሆኑም፤ የድርሰታቸውን ትርክት ግን ከሁለት “የወሐቢይዝም” ፍላጎት አኳያ መመልከት  ይቻላል። ይኸውም ቅልጥ ካለ ውሸት እና ከዓለመ አቀፍ የአክራሪነት ተልዕኮ አንፃር የሚታይ ነው።

በቅድሚያ ግን የኢትዩጵያ ሆርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ሀገራችን ውስጥ ታጥሮ የቀረ አለመሆኑን መገንዘብ ተገቢ ይመስለኛል። ምንም እንኳን የወሐቢያው እምነት አራማጅ አባባሉን በለመደ አፋቸው ሌላን ሃይማኖት ለማንጓጠጥ የተጠቀሙበት ቢሆንም፤እኔ እስከማውቀው ድረስ ቤተ-ክርስቲያኗ የዓለም ቤተ-ክርስቲያን አባል ናት። እንዲያውም ፓትሪያርኩ የዓለም አብያተ-ክርስቲያናት ፕሬዚዳንት መሆናቸው በተደጋጋሚ ሲነገር እሰማለሁ።

ታዲያ ሃይማኖቱ ‘የኢትዩጵያ ብቻ’ ከሆነ እንደምን የዓለም ቤተ-ክርስቲያናት ህብረት ፕሬዚዳንት ይሆናሉ?...ወዳጄ የወሐቢያው ደራሲ ሆይ! ይህን መሰሉን ያገጠጠና ያፈጠጠ ውሸት ለማሳመኛነት መጠቀምዎ በአሁኑ ወቅት ከሙስሊሙ ማህበረሰብ በተነጠላችሁበት ፍጥነት ልኬት ይበልጥ ከመነጠል ውጪ የሚፈይድልዎ

ምንምን ነገር የለም።…“ማን ነበር የቅሌት ቀን አይመሽም” ያለው?–እርስዎና የነውጥ ባልደረቦችዎ ትሆኑ እንዴ?…

ውድ አንባቢዎቼ! የአቶ አብደላህ “የኢትዩጵያ ሙስሊም ‘የኢትዮጵያ ብቻ’ እንዲሆኑ ይፈለጋል” የሚል ጥንቆላዊ አካሄድ የዓለም አቀፍ አክራሪነት ሽኩቻን አስፈፃሚ የመሆን ፍላጎትንም ያዘለ ነው። አንድ ሃይማኖት ነባር እሴቱን ትቶ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተውን የፅንፈኝነተ አስተሳሰብ መከተል አለበት ማለት፤የሌሎች የእምነት ነፃነት በመፃረር “እኛን ብቻ ተከተሉ” የሚል ፍላጎት በውስጡ አንግቧል።

ታዲያ ይህ “የወሐቢይዝም” ሰነድ ያረጋገጠልን አንድ ሃቅ ቢኖር፤ በተደጋጋሚ በሙስሊሙ ዘንድ ፅንፈኞቹ ሀገራችን ውስጥ እንዲፈፀም የሚፈለገው የአክራሪነት ሽኩቻ “አንድ ክንፍ ናቸው” የሚለው መነጋገሪያ አጀንዳ ትክክል መሆኑን ነው። ምክንያቱም ልክ እንደ ኢትዩጵያ ሆርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ሁሉ፤ ከዓለም አቀፍ ይእስልምና ተቋማት ጋር በጥምረት የሚሰራውንና የተለያዩ የሃጅና ዑምራ ጉዞዎችን የሚያከናውነውን መጅሊስ በማጣጣል፤‘ፅንፈኛ ሆነን ለምን ከአክራሪዎች ጋር አልተባበርንም’ ማለት የተቀጠሩበትን የተላላኪነት ተግባር መወጣት ስለሆነ ነው።

በ‘እንዲህ ሊሆን ይችላል’ አጉል መላ-ምት የታጨቀው “ድርሳነ-ወሐቢያ” ሃፍረት ለምኔ ነው። እንዲህም ይላል–“ተማሪዎችና የመንግስት ሰራተኞች ትምህርትንና ስራን ያስተጓጉላል በሚል በሮመዳን ወቅት እንዳይፆሙ ሊደረጉ ይችላሉ።”…ታዲያ አሁን የምንገኘው በቅዱሱ የሮመዳን ወቅት በመሆኑ ይህን አባባል ለአፍታ አሰብኩት።… እናም በአንድ ወቅት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ “…ሳስበው ሳስበው ደከመኝ” በማለት ለፓርላማ ያቀረቡትን ተረት ከማስታወስ ውጪ፤ በወሐቢያው ሰነድ የተጠቀሰው “ተማሪዎችና የመንግስት ሰራተኞች እንዳይፆሙ ይደረጋሉ” የሚለውን የጥንቆላ ንግርት ፈልጌ ላገኘው አልቻልኩም።

እርግጥም አንድ ዴሞክራሲያዊ መንግስት በዜጎቹ ሃይማኖት ውሰጥ ገብቶ “እንዳትፆሙ” ይላል ብሎ ማሰብ መሰረቱ እውነት የሆነን ሃይማኖት እተላለሁ ከሚል ግለሰብ የሚጠበቅ አይመስለኝም– ግለሰቡ የአዕምሮ ችግር ከሌለበት በስተቀር። እናም ይህን መሰሉን የሌለን ሁኔታ እንዳለ በማስመሰል ለማጭበርበር ማቅረብ ሃፍረትን አከናንቦ “ድንቄም ሃይማኖተኛ” በመባል የውሸት ፖለቲካ ተንታኝ ከመሆን የዘለለ ስያሜ አያሰጥም። ለምን ቢሉ፤ይህን መሰሉ የቅዥት አስተሳሰብ “በወሐቢይዝም” አቀንቃኞች አዕምሮ ውስጥ እንጂ በተጨባጭ በምናውቃት አዲሲቷ አትዩጵያ ውስጥ ታይቶም ሆነ ተሰምቶ ስለማይታወቅ ነው።

እንዲያውም አሁን በምንገኝበት የሮመዳን ፆም ወቅት ክርስቲያን ተማሪዎችና ሰራተኞች “የጿሚዎችን ስራ እኛ እንሸፍናለን” በማለት እያገዙን ነው። እናም እነዚህን መሰሎቹ እውነታዎች የወሐቢያው “አትፁሙ ትባላላችሁ” ተረት አቀንቃኞችን ውሸት የሚያጋልጡ ህያው ምስክሮች ናቸው ማለት ይቻላል።

በሰነዱ ላይ የተጠቀሰው ሌላኛው ጉዳይ የኢትዩጵያ መንግስት የምዕራባዊያንን ፍላጎት የሚያስፈፅም አስመስሎ የመግለፅ ሁኔታ ነው። ይሁን እንጂ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው የሀገራችን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት የራሱ የሆኑ ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ አቅጣጫዎች ያሉት ሲሆን፤ ከሚከተለው መስመር ውጪ የየትኛውንም ሀገር ጣልቃ ገብ ተፅዕኖ የሚቀበል አይደለም። በሀገሩ የውስጥ ጉዳይ ወሳኙ ሃይል እንዲያስተዳድረው ኮንትራት የሰጠው ህዝብ እንጂ የውጭ ሃይሎች አለመሆናቸውን በፅናት የሚያምን ነው። አዎ! የኢፌዴሪ መንግስት የሀገሩን ብሔራዊ ጥቅም ከማስጠበቅ ባለፈ፤የህዝቡን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት በይፋ በማረጋገጥ ማንነታዊ ባህሪው የሚታወቅ መሆኑን በምስጢራዊ ሰነዶቹ ጭምር ተመስክሮለታል።

ዲፕሎማሲያዊ ሰነዶችን አነፍንፎ ይፋ በማድረግ የሚታወቀው “ዊኪሊክስ” የተሰኘው ድረ-ገፅ በአንድ ወቅት በኢትዩጵያ የአሜሪካ አምባሳደር የነበሩት ቪኪ ሃድሰንን ዋቢ አድርጎ እንደገለፀው፤ “የኢትዩጵያ ባለስልጣናት የሀገራቸውን ጥቅም ብቻ የሚያስጠብቁ ናቸው” ብሏል። ይህ ገለልተኛ ምስክርነት በግልፅ እንደሚያመላክተው የሀገራችን መንግሰት ከህዝቡ ውጪ የሚያዘው አንዳችም ሃይል የሌለ መሆኑን ነው። እናም

የወሐቢያው ሰነድ ይህን ዕውነታ እያወቀ፣ሆን ብሎ ያላወቀ በመምሰል የኢትዩጵያ መንግስት የሌሎችን ተግባር ይከውናል እያለ ለማላዘን መሞከሩ ከተራ አሉባልታነት የሚዘል አይሆንም።

“ድርሳነ-ወሐቢያ” እጅግ አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ የመንግስት ባለስልጣናትንና ሰራተኞችን ስም እየጠቀሰ ባላቸው እምነት ምክንያት ሊኮንናቸው ሞክሯል። በተለይም የክርስትና እምነት ተከታይ የሆኑ ግለሰቦችን እየጠቀሰ የእነርሱን እምነት የመንግስት ሃይማኖት አድርጎ ለማቅረብ ይጥራል። ይሁንና አንድ የመንግስት ተቀጣሪ ባለስልጣን እንደ ማንኛውም ግለሰብ ‘የራሱ ሃይማኖት ለምን ኖረው?’ ተብሎ ሊጠየቅ አይችልም። ባለስልጣኑ ክርስቲያን አሊያም እስላም ቢሆንም እምነቱን በመንግስትና በድርጅት ውስጥ ለማስረፅ እስካልሞከረ ድረስ የእምነት ነፃነቱ እንደማንኛውም ዜጋ ይከበርለታል።

ወትሮም ቢሆን የግለሰቦችን የእምነት ነፃነት ለመድፈቅ የተሰለፈው “ወሐቢይዝም” ግን ይህን ዕውነት ለመቀበል አይፈልግም። ከዚህ በዘለለም የመንግስት ተቀጣሪ ባለስልጣናትን ስም እየጠራ “መንግስት የክርስትና የበላይነት የነገሰባት ኢትዩጵያን መገንባት ይፈልጋል” በማለት ከህገ-ምንግስታዊ ድንጋጌ ውጪ የሆነን ልቦለዳዊ ድርሰት ለማነብነብ ይሻል። ግና ድርሳኑ ምንም ይበል ምን፣ የማንኛውም ሃይማኖት የበላይነት ኢትዩጵያ ውስጥ ሊኖር አይችልም። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ የለየለት ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ከአፄውና ከደርግ መንግስታት ጋር አብሮ የተረሳ ስለሆነ ነው።

እርግጥ የአቶ አብደላህ ፍላጎት ‘እኛ ወሐቢያዊያን የበላይ መሆን አለብን’ የሚል ከሆነ፤የቀን ቅዠታቸው “ላም አለኝ በሰማይ…” እንዲሉት መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ለምን ቢሉ፤ሃይማኖትና መንግስት በተለያዩበት ሀገር ውሰጥ የክርስቲያንም ይሁን የእስልምናን ሃይማኖት የበላይነት ማስፈን ማለት ህገ-መንግስቱን ቀድዶ የመጣል ያህል የሚቆጠር ነው። ይህ ደግሞ የኢትዩጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች እስካሉ ድረስ ከቶም ሊታሰብ የሚችል አይደለም።

መቼም በድርሳኑ ላይ መንግስት በጭፍን ጥላቻ ያልተብጠለጠለበትን ቦታ ፈልጎ ማግኘት አይቻልም። “መንግስት ሙስሊሙ ከኢትዩጵያ ፖለቲካ እንዲነጠል ይፈልጋል” የሚለው አሉባልታ ሌላኛው አስቂኝ ድራማው ነው።

ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ንደው ኢስላማዊ መንግስት የመመስረት ቀቢፀ-ተስፋን ያነገቡት የሰነዱ ባለቤት(ቶች)፤ ይህን መሰሉ ፀረ-ህገ-መንግስታዊ አስተሳሰብ ማቀንቀናቸው የሚገርም አይደለም። ምክንያቱም ዓላማቸው ማንም በገሃድ የሚያውቀውንና ሙስሊሙ ህብረተሰብ እንደ ማንኛውም ዜጋ በሀገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ እኩል ተሳታፊ መሆኑን በመካድ ተዓማኒነት የሌለው ተራ የፖለቲካ ትርፍ ማግኘት ስለሆነ ነው። ሆኖም የሀገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር ለሙስሊሙም ይሁን ለሌላው እምነት ተከታይ ክፍት መሆኑን በአሁኑ ወቅት በሂደቱ ተሳታፊ የሆንነው የእምነቱ ተከታዩች ስልምናውቀው በዘ መልኩ ምዕመኑን ማደናገር እንደማይቻል እነ አያ “ቆርጦ ቀጥል” ሊያውቁት ይገባል።

በመሆኑም ‘ሙስሊሙ ከሀገሪቱ ፖለቲካ ተነጥሏል’ በሚል የቅጥፈት ድርሰት ፅንፈኛው “ወሐቢይዝም” ፍላጎቱ እግረ-መንገዱን ኢስላማዊ መንግስት መስርቶ ዙፋን ላይ መንጠላጠል ከሆነ፤ ይህ የእብደት ሃሳብ ሊሳካ እንደማይችል መረዳት ያሻል። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ መንግስትንና ሃይማኖትን ደባልቆ የሸሪዓ አስተዳደርን ለመመስረት ማሰብ፤ ሀገሪቱ ከምትከተለው የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት ጋር በቀጥታ የሚጣረስ በመሆኑ ነው። እናም የድርሳኑ ከታቢ ወይም አስከታቢያቸው ይህ ፀረ-ህገ-መንግስታዊ ፍላጎታቸው የሚሳካው በህልም እንጂ በገሃዱ ዓለም ውስጥ ሊሆን አይችልም–ፀባቸው በቀጥታ ከህዝብ ጋር ነውና።

“ድርሳነ-ወሐቢያ” ያለ አንዳች ሃፍረት የገለፀው ሌላኛው ነጥብ “የመንግስት ባለስልጣናት አህባሽን ይደግፋሉ” የሚል ነው። ሆኖም እኔ እንደ አንድ ሙስሊም እስከሚገባኝ ድረስ “አህባሽ” የሚባለውን እምነት አላውቀውም። እርግጥ ኢትዩጵያ ውስጥ ከነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ ነባር የእስልምና እምነትን አውቃለሁ። በአሁኑ ወቅትም በተለያዩ የውጭ ሃይሎች ደጋፊነት አክራሪነትን የሚያጧጧፉትን

ወሐቢያዎችንም እንዲሁ። ከዚህ ውጪ ፅንፈኞቹ “አህባሽ” እያሉ የሚጠሩት እስልምና ሊገባኝ አይችልም– ከነባሩ እስልምና በስተቀር።

ያም ሆነ ይህ ግን፣ የኢትዮጵያ መንግስት ከህገ-መንግስታዊ ድንጋጌው ውጪ የትኛውንም የእምነት ወገን (sect) ሲደግፍም ሆነ ሲያጣጥል አይተንም ሆነ ሰምተን አናውቅም። መንግስት በመላ ሀገሪቱ ህግና ስርዓትን ከማስከበር ባለፈ፣ የትኛውንም ሃይማኖት ደግፎ አሊያም በተቃራኒው ቆሞ ተግባሩን ሊወጣ አይችልም። ለምን ቢባል፤ቀደም ባሉት ፅሑፎቼ ደጋግሜ እንደገለፅኩት መንግስት በሃይማኖት፣ሃይማኖትም በመንግስት አሰራሮች ውስጥ ጣልቃ ሊገቡ የሚችሉበት አንዳችም ቀዳዳ ባለመኖሩ ነው።

እናም መንግስት ‘እገሌ የሚባል እምነትን ይደግፋል’ ተብሎ የቀረበው የአክራሪዎች ተረት፤‘ፅሑፉ የእኔ ነው’ ያሉት ግለሰብ የሚገኙበት የፅንፈኞች ቡድን ፍላጎት አልፋና ኦሜጋ ግቡ ፖለቲካዊ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ይህም ወሐቢያ ከሃይማኖት ጋር ሆድና ጀርባ ስለመሆኑ ሁነኛ አስረጅ ነው። ለዚህም ነው አስፀያፊ በሆነ ሁኔታ የመንግስት ተቀጣሪ ባለስልጣናትን ስም እየጠቀሰ ‘እገሌ ሃይማኖቱ ክርስቲያን ስለሆነ እስልምናን ያዳክማል’ በማለት የጅምላ ፍረጃን በመጠቀም ፖለቲካዊ ፍላጎቱን ለማሳካት ከወዲያ ወዲህ ሲዳክር የምናየው።

ወሐቢያ ዓላማው ሃይማኖታዊ መብትን ማስጠበቅ ቢሆን ኖሮ፤ በ73 ገፅ ሙሉ ፅሑፉ የመንግስት ፖሊሲዎችንና ተቀጣሪዎችን እንዲሁም የፓርቲ ልሳኖችን ‘በእንዲህ ሊሆን ይችላል’ የደፈና መላ-ምት ለማውገዝ ባልቋመጠ ነበር። ግና ፍላጎቱ “ፍየል ወዲህ፣ ቅዝምዝም ወዲያ” መሆኑን እንድናውቀው አድርጎናል። እናም ምስጋና ለአክራሪዎቹ ፀሐፊ ይሁንና ሁሉንም እኩይ ምግባራቸውን አንድ በአንድ ተገንዝበነዋል። አዎ! “ወሐቢይዝም” የፖለቲካ እንጂ የሃይማኖት ቡድን አለመሆኑን ልቅም አድርገን ተረድተናል።…ድንቄም የእስልምና ተሚጋች!...

ውድ አንባቢዎቼ! በአቶ አብደላህ አደም ተኪ ስም ‘ይሆናል፣ተብሎ ይገመታል…ወዘተ’ በሚሉ መላ-ምቶች የቀረበውና እኔም “ድርሳነ-ወሐቢያ” በሚል ርዕስ በአራት ተከታታይ ክፍሎች በወፍ በረር የቃኘሁት አስገራሚ ጥራዝ አንኳር ነጥቦች ይህን ይመስላሉ።

ታዲያ ግለሰቡም ይሁኑ ያስፃፋቸው ፅንፈኛ ቡድን በ ‘ሊከሰት ይችላል’ ፅሑፍ የሚያመላክተን ቁልፍ ጉዳይ ቢኖር፤ የወሐቢያ አቀንቃኞች የሚከተሉት ወይም ሊከተሉ የሚችሉት አደገኛ ኢ-ህገ-መንግስታዊ አካሄድን ነው።ይኸውም በሃይማኖት ከለላነት ሁከትና ብጥብጥን በመፍጠር የተረጋጋውን ሰላማችንን ማናጋትና ሀገራችን እያስመዘገበች ያለውን ዕድገት የኋሊት ለመቀልበስ መጣር ነው።

ዳሩ ግን ኢስላም የሰላምና የፍቅር እምነት መሆኑን የምናውቀው እኛ ሙስሊሞች ደግሞ እነዚህን ወገኖች በማጋለጥ አደብ ልናስገዛቸው ይገባል። በመሆኑም ሰላማችንንና ዕድገታችንን በየመስጂዱና በየመንደሩ ለማወክ የሚጥሩትን አስፀያፊ ተግባራት እንዲሁም እንደ አቶ አብደላህ ዓይነት በሃይማኖት ስም ውሸት በመቀመር ወረቀት የሚበትኑ ጥቂት ግለሰቦችን በማውገዝ ከመካከላችን እንዲነጠሉ ማድረግ ይኖርብናል። ሮመዳን ሙባረክ!